# በፀሐይ ሐይል አማካይነት የኤሌክትሪክ ክፍያዎን መቆጠብ ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሐብት ይወቁ።

ነዋሪዎች የፀሐይ ፓነሎችን በቤታቸው መግጠም ባይችሉም፣ ከፀሐይ ሃይል መጠቀም ይችላሉ። እኛ - የዲሲ መንግስት - ቤት ባለቤቶችና ተከራዮች ከማህበረሰብ የፀሐይ ሃይል ፕሮጀክት ኤሌክትሪክ ሲያገኙ **ወደ $500 የሚሆን ቅናሽ** በማቅረብ ከኤሌክትሪክ ክፍያቸው ላይ እንዲቀነስ አድርገናል። በዲስትሪክቱ በሙሉ በሚገኙት ህንጻዎችና ቤቶች ሃይል ለመስጠት የማህበረሰብ የፀሐይ ሃይል ፕሮጀክቶችን እንገነባለን።

ይህ ፕሮግራም Solar for All ይባላል እናም የቀረበው በ Department of Energy & Environment (DOEE፣ የሃይል እና አካባቢ ክፍል) እንዲሁም በ DC Sustainable Energy Utility (የዲሲ የዘላቂ ሃይል ፍጆታ) በኩል ነው።

## ብቁ መሆንዎን ያጣሩ።

እነዚህ **ሁሉ** መግለጫዎች እውነት ከሆኑ እርስዎ ብቁ ነዎት፡

- በዲሲ ውስጥ ወይ ቤት ተከራይተዋል አልያም የራስዎ ቤት አለዎት።
- የእርስዎ ስም ወይም በቤተሰብዎ ስም ያለ የሆነ ሰው በ Pepco የኤሌክትሪክ ሂሳብ ላይ ሰፍሯል።
- እርስዎ ቢያንስ 18 አመትዎ ነው (ወይም ከ 18 አመት በታች ሆነው ነገር ግን ከወላጆችዎ/ከአሳዳጊዎችዎ ቁጥጥር ነጻ ነዎት)።
- እና ከእነዚህ መግለጫዎች ውስጥ አንዱ  እውነት ከሆነ፡
    - ቤተሰብዎ የፍጆታ ድጋፍ ያገኛል ወይም ከእነዚህ ፕሮግራሞች በአንዱ ድጋፍ እንዲያገኝ ይደረጋል። ተጨማሪ የምግብ ድጋፍ ፕሮግራም (SNAP)፣ ጊዜያዊ ድጋፍ እርዳታ ለሚፈልጉ ቤተሰቦች (TANF)፣ ተጨማሪ የደህንነት ገቢ (SSI)።***ወይም***

- የቤተሰብዎ አመታዊ ጠቅላላ ገቢ— ታክስ ከመክፈልዎት በፊት ያለው ገቢ — በቤተሰብዎ መጠን መሰረት ከገደቡ በታች ወይም እኩል ነው። ገቢን ለማስላት፣ ከሚኖሩበቻው ወጣቶች ጋር ያለን በስራ የተገኘ ገንዘብ ታክስ ከመክፈልዎ በፊት ይደምሩ። ከዚያም፣ ከማህበራዊ ደህንነት፣ ከስራ አጥነት፣ ከልጅ ድጋፍ ወይም ከጡረታ ክፍያዎች የሚገኙትን አብረዎት ከሚኖሩት ማንኛውንም ሰዎች የተገኘ ገንዘብ ይደምሩ። (ከ 18 አመት በታች የሆኑ ልጆችን ያጠቃልላል)። ከዚህ በታች ምልክት ያኑሩ።

| **የቤተሰብ መጠን** (ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውንም ሰው ይቁጠሩ) | **ከፍተኛው የቤተሰብ ገቢ** |
|---|---|
| 1 | $70,600 |
| 2 | $80,650 |
| 3 | $90,750 |
| 4 | $100,800 |
| 5 | $110,900 |
| 6 | $121,000 |
| 7 | $131,050 |
| 8 | $141,150 |
| 9 | $151,200 |
| 10 | $161,300 |

# ያመልክቱ።

1. ፎቶ ያለባቸው መታወቂያ ካርዶችን (እንደ መንጃ ፈቃድ ያሉ) ለእርስዎና ለቤተሰቦችዎ አባላት ይሰብስቡ። በሚያመለክቱበት መንገድ ላይ በመመስረት፣ መታወቂያዎን ኮፒ ሊያደርጉ ወይም ስካን ሊያደርጉ ይችላሉ።

2. በኦንላይን ለማመልከት ከእነዚህ ምርጫዎች አንዱን ይምረጡ፣ በኢሜይል ወይም በፖስታ፡
   - የአንላይን ማመልከቻ ይሙሉ።
   - ማመልከቻዎን በእንግሊዝኛ ወይም በስፓኒሽ ለsolarforall@dc.gov ኢሜይል ያድርጉ። ኢሜይሉ ላይ የሰነዶችዎን ፎቶ ወይም ስካን ማያያዝ ይኖርብዎታል።
   - ማመልከቻዎን ፕሪንት አድርገው በእንግሊዝኛ ወይም ስፓኒሽ ከስር ወዳለው አድራሻ ይላኩ። ሰነዶችዎን ኮፒ ማንሳት አለብዎት። እባክዎን ኦሪጅናል ሰነዶቹን አይላኩ።

DOEE Solar for All
810 1st Street NE, 9th Floor
Washington, DC 20002

በማንኛውም ጊዜ ማመልከት ይችላሉ።

# የበለጠ መረጃ ይሰብስቡ።

## ካመለከትኩ በኋላ ምን ይፈጠራል?

1. በ 5 የስራ ቀናት ውስጥ፣ እኛ —የዲሲ መንግስት— ማመልከቻው ተቀባይነት እንዳገኘ ወይም ማመልከቻዎን ለማጽደቅ ተጨማሪ መረጃ መፈለጋችንን በስልክ በመደወል ወይም በኢሜይል እናሳውቀዎታለን። ስላማመልከቻዎ አዲስ ነገር ለማግኘት በ (202) 299-5271 ላይ መደወል ይችላሉ።

2. የገቢዎትን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በቅድሚያ መረጃዎቻችንን እናጣራለን። ገቢዎን ለማረጋገጥ ከእርስዎ ተጨማሪ መረጃ የምንፈልግ ከሆነ፣ በየደረጃዎቹ እንዲያልፉ በማድረግ ፍጆታዎችዎን በተጨማሪ እንዲከፍሉ የሚረዳውን የዝቅተኛ ገቢ የቤት የሃይል እርዳታ ፕሮግራም (LIHEAP) እንዲያመለክቱ እናደርጋለን።

3. ማመልከቻዎ እንደጸደቀ፣ እርስዎን ለማህበረሰብ የፀሐይ ሃይል ፕሮጀክቶች እንመዘግብዎታለን እንዲሁም ለእርስዎ የኤሌክትሪክ መለያ ክሬዲት እንዲጨመርልዎ ከ Pepco ጋር በጋራ እንሰራለን። በማህበረሰባችን የፀሐይ ሃይል ፕሮጀክቶች ላይ በመመስረት፣ አንድ ቦታን ለመክፈት ከ 3-6 ወራት ሊፈጅ ይችላል። ጉዳዩ ያ ከሆነ፣ እርስዎን ለማሳወቅ እንደውላለን ወይም ኢሜይል እናደርግልዎታለን።

4. ለማህበረሰብ የፀሐይ ሃይል ፕሮጀክት ከመዘገብንዎ በኋላ፣ በ 1-2 የፍጆታ ክፍያ ዙሮች ውስጥ በ Pepco ፍጆታዎ ላይ አንድ ክሬዲት ማየት ይጀምራሉ።

ካልጸደቀልዎ፣ በገበያ ዋጋዎች እንዴት ወደ ፀሐይ ሃይል አቅራቢነት እንደሚቀየሩ በስልክ ወይም በኢሜይል ከመረጃ ጋር እናሳውቅዎታለን። በእኛ ውሳኔ ካልተስማሙ፣ ይግባኝ እንዴት እንደሚጠይቁ እናሳይዎታለን።

**ሁሉም ብቁ አመልካቾች ቅናሹን ያገኛሉ?**

አዎ፣ ነገር ግን የፀሐይ ሃይልን ማግኘት ለመጀመርና ከኤሌክትሪክ ፍጆታዎ ላይ ገንዘብ ለመቆጠብ በማህበረሰብ የፀሐይ ሃይል ፕሮጀክቶች ላይ ተመስርቶ፣ ከ 3-6 ወራት ሊፈጅ ይችላል።

**ማወቅ ያሉብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?**

ከኤሌክትሪክ ፍጆታ ላይ ገንዘብ መቆጠብን ለመቀጠል ከፈለጉና የፀሐይ ሃይል ማግኘት ከፈለጉ፣ በየሶስት አመቱ የቤተሰብዎን ገቢ ማረጋገጥ አለብዎት። እኛ —የዲሲ መንግስት— አሁን ያለዎት ቅናሽ የአገልግሎት ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት የማስታወሻ ኢሜይል ወይም ደብዳቤ እንልክልዎታለን። ገቢዎን ካላረጋገጡልን፣ ነጻ የፀሐይ ሃይል ማግኘትዎ ይቆማል። የማሳወቂያ ኢሜይሉ ወይም ደብዳቤው የሚያጠቃልለው ቀላል ቅጽ እና መመሪያዎችን ነው።

ገቢዎ ከፕሮግራሙ ገደብ በላይ ከጨመረ፣ገቢዎ በጨመረበተ በ 60 ቀናት ውስጥ በ solarforall@dc.gov ላይ ወደ እኛ ኢሜይል ማድረግ ወይም በ (202) 299-5971 ላይ እኛ ጋር መደወል አለብዎት።

**ጥያቄዎች ካሉኝ ማንን ማነጋገር አለብኝ?**

መጀመሪያ፣ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን በገጹ የታችኛው ስፍራ ላይ ይመልከቱ። አሁንም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን ለሁሉም የስልክ መስመሮች የእኛን Solar for All

የስልክ መስመር በ(202) 299-5271 ላይ ከሰኞ እስከ አርብ ከ 9 am እስከ 5 pm ባለው ጊዜ ያግኙን። ወይም የSolar for All ቡድንን በsolarforall@dc.gov ላይ በ ርእሰ መስመር “Community Solar Question” በማለት ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

**ቤቴን የበለጠ ለአካባቢ ተስማሚ ለማድረግ አሁንም ቢሆን እርዳታ ያስፈልገኛል። ምን ማድረግ አለብኝ?**

በእኛ የፍጆታ ሀብቶች ገጽ ላይ እርዳታ ሊያደርጉ ስለሚችሉ ሌሎች ሃብቶች መረጃ ማግኘት ይችላሉ። በተጨማሪም ቤትዎን የበለጠ ለአካባቢ ተስማሚ ለማድረግ ስላሉት ሃብቶች ማወቅ ይችላሉ።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ከማህበረሰብ የፀሐይ ሃይል ፕሮጀክት ኤሌክትሪክ ሳገኝ ምን ያህል ገንዘብ እቆጥባለሁ?**

ማመልከቻው እንደጸደቀ፣ እኛ —የዲሲ መንግስት— ከ PEPCO ጋር በመስራት ወደ ኤሌክትሪክ መለያዎ አንድ ክሬዲት እንጨምራለን። ከኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያዎ ላይ በአመት $500 ያህል ይቆጥባሉ። ወደ ፀሐይ ሃይል ለመቀየር ምንም ተጨማሪ ክፍያ መክፈል አይጠበቅብዎትም።

በተጨማሪ ለዝቅተኛ ገቢ የቤት ሃይል እርዳታ ፕሮግራም (LIHEAP) ከተቀበሉ ወይም ካመለከቱ፣ 30% (እስከ $475 በአመት) የሚሆን በኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያዎ ላይ በተጨማሪ መቆጠብ ይችላሉ እንዲሁም በኤሌክትሪክ፣ በጋዝ ወይም በዘይት ፍጆታዎ ላይ ተጨማሪ ክሬዲት ይቀበላሉ። በሚጠቀሙት የኤሌክትሪክ ሐይል መጠን ላይ በመመስረት፣ ለአንዳንድ ነዋሪዎች፣ ወደ ፀሐይ የመቀየራቸው ጥምር ጥቅሞች የኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያቸውን ወደ ዜሮ ያስገባዋል።

**ካልጸደቀልኝ እንደገና ማመልከት እችላለሁ?**

በቤተሰብዎ መጠን እርስዎ ክሬዲት እንዲያገኙ ለማጽደቅ፣ ገቢዎ ከገደቦቹ እኩል ወይም በታች መሆን አለበት። ገቢዎ ከተቀየረ እና ለውጡ እርስዎ ብቁ እንዲሆኑ ያደርገኛል ብለው ካሰቡ፣ በፕሮግራሙ ላይ እንደገና ማመልከት ይችላሉ።

**እኔ የቤት ባለቤት ከሆንኩና የገቢ መመሪያዎችን ካሟላሁ፣ ወደ ፀሐይ ሃይል ለመቀየር የገንዘብ እርዳታ የማገኝበት ሌላ መንገድ አለ?**

አዎ። በአንድ ቤተሰብ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ ወይም አራት ወይም ከዚያ በታች ክፍሎች ባለው ሕንጻ ላይ የሚኖሩ ከሆነ፣ የፀሐይ ፓናሎች ከጣራዎ ስር በነጻ ተገጥሞ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

**የማህበረሰብ የፀሐይ ሃይል ፕሮጀክቶች የሚሰሩት እንዴት ነው?**

የፀሐይ ፓናሎች ከፀሐይ ሃይል ይስቡና እርስዎ ሊጠቀሙበት ወደሚችል ኤሌክትሪክ ይለውጡታል። ለማህበረሰብ የፀሐይ ሃይል ፕሮጀክቶች፣ ኤሌክትሪኩ ወደ ፍርግርጉ በመተላለፍ፣ በዲስትሪክቱ ያሉ ቤቶችን ሃይል እንዲያገኙ ያደርጋል። በዲስትሪክቱ ባሉት የማህበረሰብ የፀሐይ ፕሮጀክቶች በመመዝገብ፣ አከራዮችና የቤት ባለቤቶች ሶላር መትከያ ጣራ ባይኖራቸውም፣ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያቸውን መቆጠብ ይችላሉ።

**የፍጆታ ክፍያዎቼን የምቆጥብባቸው ሌላ መንገዶች አሉ?**

አዎ! የዲሲ መንግስት የኤሌክትሪክ፣ የጋዝ፣ የዘይት እና/ወይም የውሃ ፍጆታ ክፍያዎን ለመቆጠብ ብዙ ሀብቶችን አቅርቧል።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ኤፕሪል 2021 ነው።*